የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አፈፃፀም ክትትል ሪፖርት በጉምሩክ ኮሚሽን

ጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMMISSION

የክትትል ሪፖርት

ጥር 2014 ዓ.ም.

ማውጫ.. i
ምስጋና iii
ክፍል አንድ 1
1. መግቢያ 1
1.1 ዳራ 1
1.2 የክትትሉ ዓላማ 2
1.2.1 አጠቃላይ ዓላማ 2
1.2.2 ዝርዝር ዓላማዎች 2
1.3 የክትትሉ አስፈላጊነት 2
1.4 የክትትሉ ስልት 3
1.4.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ 3
1.4.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ 4
1.5 የክትትሉ ወሰን 5
1.6 የክትትሉ ውስንነት 5
ክፍል ሁለት 6
2. ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር 6
2.1 አደረጃጀት 6
2.2 የጉምሩክ ኮሚሽን አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት 10
2.2.1 የአቤቱታ ወይም ቅሬታ ማቅረቢያ መንገዶች 11
2.2.2 የአስተዳደራዊ ውሳኔ ዓይነቶች 12
3. የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት 16
3.1 የቀረጥና ታክስ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ 16
3.1.1 አቤቱታ አቀራረብ 16
3.1.2 አቤቱታ በጽሁፍ እንዲቀርብ ከማድረግ አንጻር 17
i. ጉዳዩን ስለመስማት 17
3.1.4 የአስተዳደር ውሳኔ ለተገልጋዩ ስለመስጠት 19
3.1.5 የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ስለማቋቋም 20
3.1.6 ቅሬታውን ስለመመርመርና ስለመወሰን 21
3.1.7 ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለማሳወቅ 23
3.2 ከታክስ ውጪ ያሉ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ 23

3.3 ስለአዋጁ ግንዛቤ በተመለከተ 24
ክፍል አራት 26
4. ማጠቃለያና ምክረ ሀሳብ 26
4.1 ማጠቃለያ 26
4.2 ምክረ ሀሳብ 28
ዋቢ ነገሮች 30
አባሪ አንድ 31
ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ዝርዝር ጥያቄዎች 31
አባሪ ሁለት 33
በጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተሰጡ የውሳኔ መዝገቦች ዝርዝር 33

ምስጋና

ይህን የክትትል ሪፖርት ስናዘጋጅ መረጃ ለመሰብሰብ የጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሄድንበት ወቅት የበላይ ኃላፊዎች ለስራ ክፍሎቻቸው አስፈላጊውን መረጃ እንዲሰጡን መመሪያ በመስጠታቸው እንዲሁም የተለያዩ የስራ ክፍሎች ደግሞ አሰፈላጊውን መረጃ በመስጠት ስለተባበሩን ልናመሰግናቸው እንወዳለን፡፡

ክፍል አንድ

1. መግቢያ

1.1 ዳራ

በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 (ከዚህ በኋላ በጽሁፉ ውስጥ አዋጁ እየተባለ የተገለጸው) መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ/ም የወጣ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር (በቀድሞ ስያሜው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ) ከዩኤስ አይዲ ፍትህ አክቲቪቲ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ጨምሮ ለፌዴራል መንግስቱ የአስተዳደር ተቋማት የበላይ አመራሮች በስልጠና መልክ አዋጁን የማስተዋወቅ ተግባር ያከናወነ መሆኑ ይታወሳል፡፡

ለአዋጁ መውጣት መሰረታዊ የሆኑ ምክንያቶችና ዓላማዎች በመግቢያው ላይ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

- በሕገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን መንግስታዊ አሰራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት የተደነገገውን ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ;[1]
- ማናቸውም የመንግስት ባለስልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን በሕገ መንግስቱ የተደነገገውን ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ;
- የአስተዳደር ተቋማት በሰዎች መብትና ጥቅም ላይ የሚያስከትሉት ጣልቃ ገብነት በሕግ የሚመራና ለሕግ የሚገዛ መሆኑን ለማረጋገጥ;[2]
- የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥና የመመሪያ አወጣጥ መርሆዎችና ሥነ ሥርዓት እንዲሁም በስተዳደራዊ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ቅር የተሰኘ ሰው በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ስርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህ ማስፈን[3] የሚሉት ናቸው፡፡

የፍትሕ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 943/2008 ከተሰጠው ስልጣን መካከል በአዋጁ አንቀፅ 6(6) ላይ በፌደራል መንግስቱ የሚወጡ ሕጎች ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ መደረጋቸውንና አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችም ስራቸውን በሕግ መሰረት መስራታቸውን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ሀላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ መሰረት በተመረጡ ተቋማትና ሕጎች

[1] የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መግቢያ የመጀመሪያው አንቀጽ
[2] የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መግቢያ ሁለተኛ አንቀጽ
[3] የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መግቢያ ሶስተኛው አንቀጽ

ላይ የተለያዩ የአፈጻጸም ጥናቶችን በመስራት ሪፖርት ሲያቀርብ መቆየቱ ታወሳል። ይህ ስራ ከዚሁ የቀጠለ የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት መደበኛ ስራ አካል ነው።

በዚህ የህግ አፈጻጸም ክትትል በጉምሩክ ኮሚሽን የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈጻጸም በተለይም ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አቀራረብ ሥርአት እና ህጋዊነት ጋር በተያያዘ ዳሰሳ ተደርጓል።

1.2 የክትትሉ ዓላማ

1.2.1 አጠቃላይ ዓላማ

የጉምሩክ ኮሚሽን በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአስተዳደር ውሳኔዎችን ሲወስን እና ቅሬታዎችን ሲሰማ በአዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ላይ የተቀመጡ መርሆዎችን ከማክበርና ከመፈጸም አንጻር ያለውን አፈጻጸም መዳሰስ ነው።

1.2.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- የጉምሩክ ኮሚሽን የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ህጋዊነት መዳሰስ
- የቅሬታ አቀራረብ፣ አሰማም እና አሰጣጥ ሂደት ህጋዊነትን መፈተሽ
- የአስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ሰሚ አካል መቋቋሙን ማረጋገጥ

1.3 የክትትሉ አስፈላጊነት

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈጻጸምን ክትትል ማድረግ አስፈላጊነት በተመለከተ በአዋጁ መግቢያ ላይ የተቀመጠውን መርሆዎች ማለትም በሕገ መንግስቱ የተደነገገውን መንግስታዊ አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት የሚያዘው በተጨባጭ ተግባራዊ ስለመሆኑ ለማየትና እንዲሁም ማናቸውም የመንግስት ባለሥልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ የሚሆንበትን አሰራር ለማምጣትና የአስተዳደር ተቋማት በሰዎች መብቶችና ጥቅሞች ላይ የሚያሳርፉት ወሳኔ በሕግ የሚመራ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ አንዱ ማሳያ መንገድ ነው።

ከዚህ አንጻር የጉምሩክ ኮሚሽን፦

- ባንድ በኩል የሚያስፈጽማቸው ህጎች እና የሚያስተላልፈው ውሳኔ በአብዛኛው ከወጪና ገቢ ንግድ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ በማስከፈል የህዝብና የመንግስት ጥቅም የማስከበር ተግባር መወጣት የሚጠበቅበት በመሆኑ ፣
- በሌላ በኩል ደግሞ ምቹና የተቀላጠፈ የጉምሩክ አሰራር በመዘርጋት በዘርፉ የተሰማሩ ተገልጋዮች ያለአድሎ በፍትሃዊነት የማስተናገድ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣

በዚህ አግባብ የሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ወጥነት፣ ተገማችነትና ከአድሎዊ አሰራር የጸዱ እንዲሆኑ በማድረግ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች ተገቢውን ቀረጥና ታክስ በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲከፍሉ የሚያደረግ የሞራል ልዕልና በመፍጠር ለሀገር እድገትና ልማት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን ለማሳካት ደግሞ አስተዳደራዊ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በአዋጁ የተቀመጡ ሂደቶችን ማክበርና መፈጸም ጠቀሜታው የጎላ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት የጉምሩክ ኮሚሽን ተቋም ስለአዋጁ ግንዛቤ እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ የአፈጻጸም ክፍተት በታየባቸው ጉዳዮች መንስኤውን በመለየትና የመፍትሔ ሃሳብ በመስጠት የወደፊት ስራቸውን በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ መሰረት እንዲመሩ ያግዛል።

1.4 የክትትሉ ስልት

1.4.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ይህን ክትትል ለማዘጋጀት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅመናል።

1.4.1.1 የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጭ

ሀ.የሕግ ዳሰሳ

የጉምሩክ ኮሚሽን የሚያስፈጽማቸው ሕጎች በተለይ ለሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት የሆኑ የታክስ ሕጎች ለዚህ ጥናት ግብዓት እንዲሆኑ በጥልቀት ተዳሰዋል።

ለ. ቃለ መጠይቅ

ይህን የአስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም ሪፖርት ለማዘጋጀት በገቢዎች ሚኒስቴር የሚገኙ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ቃለ መጠይቅ አድርገናል። እንዲሁም የቡድን ወይይት አድረገናል። በመሆኑም በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት መሰረት ያገኘነውን መረጃ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት ተጠቅመንበታል።

ሐ. ምልከታ

የጥናት ቡድኑ መረጃ ለመሰብሰብ ወደጉምሩክ ኮሚሽን ዋናው መስሪያቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሄደበት ወቅት በኦንላይን የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተለይም የኦንላይን አቤቱታ አቀራረብና አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ምልከታን እና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን እንደ አንድ መረጃ ግብዓት በመውሰድ ተጠቅመንበታል፡፡

1.4.1.2 ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ

መ.ሰነዶች

ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የአቤቱታ አቀራረብ ቅጾችን፣ የውሳኔ ናሙናዎችን፣ አሃዛዊ መረጃ የያዙ ሰነዶችን ለመረጃ ግብዓት ተጠቅመናል፡፡ እንዲሁም የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ማብራሪያ ሰነድ ለጥናቱ እንደ አንድ ግብዓት ወስደናል፡፡

1.4.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ

የተከተልነው የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ዓላማ-መር (purposive sampling) የናሙና አወሳሰድ ዘዴን ተጠቅመናል፡፡ ይህን የመረጃ አወሳሰድ ዘዴ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ለማግኘት ስለሚያስችል ነው፡፡

- በአጠቃላይ የተቋሙን አሰራር ሊወክል ይችላል ያልናቸውን የጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት እና ከቅርንጫፍ ጽቤቶች በአብዛኛው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚከናወንባቸውን የአዲስ አበባ ቃሊቲ፣ የአዲስ አበባ ኤርፖረት፣ ሞጆ እና አዳማ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተለይተዋል፡፡ የኮሚሽኑ የውስጥ አደረጃጀት ሰነድ እንደመነሻ በመውሰድ ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር ይበልጥ ቁርኝት ያላቸውን የተቋሙን የተለያዩ የስራ ሂደቶችን ለይተናል፡፡
- የስራ ኃላፊነትና ሙያን መሰረት በማድረግ በተሟላ ሁኔታ መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን ለቃለ-መጠይቅ በራሳችን መርጠናል፡፡ እንዲሁም ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሰነዶችን ለመረጃ ግብዓትነት ወስደን አይተናል፡፡

1.5 የክትትሉ ወሰን

ይህ ሪፖርት የጉምሩክ ኮሚሽን በተለያዩ ህጎች አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባር ሲያከናውን የአስተዳደር ሥነ-ሥርአት አዋጁ ያስቀመጣቸውን የስነ-ስርአት እና ህጋዊነት መርሆች ተከትሎ ስለመሆኑ ብቻ የሚዳስስ እንጂ የኮሚሽኑን አበይት ስራ በተመለከተ ያለውን አፈጻጸም የሚሸፍን አይደለም፡፡ ከጊዜ አንጻር የአስተዳደር ሥነ-ሥርአት አዋጁ ጸድቆ በስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ብቻ የቃኘ ነው፡፡ በመጨረሻም ምንም እንኳን የአስተዳደር ሥነ-ሥርአት አዋጁ የሚገዛው የመመሪያ አወጣጥ እና አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እና ህጋዊነትን ቢሆንም በዚህ ክትትል የኮሚሽኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣ ሂደት እና ህጋዊነት አፈጻጸም ብቻ ተዳሷል፡፡ ይሁን እንጂ ለአንባቢዎች መረጃ ለመስጠት በማሰብ ከመመሪያ አወጣጥ አንጻር የኮሚሽን መስሪያ ቤቱን ሚና እና በዚህ ሪፖርት ውስጥ በዝርዝር ያልተካተተበትን ምክኒያ ጠቀሞ ለማለፍ ተሞክሯል

1.6 የክትትሉ ውስንነት

- አስፈላጊውን መረጃ በተሟላ አኳኋን አለማግኘት ችግር ያጋጠመ ቢሆንም በተደጋጋሚ በመጠየቅና የተቋማቱን ድህረ-ገጽ በማየት በዚህ ረገድ የታየውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡
- የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በእኛ ሀገር አዲስ ጽንሰ ሀሳብ በመሆኑ ሊጠቀስ ወይም ምሳሌ ሊሆን የሚችል አስቀድሞ የተሰሩ ስራዎች ባይኖርም አዋጁንና የማብራሪያ ሰነዱን እንደመነሻ ተጠቅመናል፡፡
- የጊዜ እጥረት ቢኖርም የእረፍት ጊዜን በመጠቀም ለማካካስ ተሞክሯል፡፡
- የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጥናቱ አለመሳተፋቸው;

ክፍል ሁለት

2. ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር

2.1 አደረጃጀት

የጉምሩክ ኮሚሽን በቀድሞ ፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1097/2008 አንቀጽ 31(2) መሰረት አሁን የያዘውን ስያሜና አደረጃጀት ከመያዙ በፊት በአዋጅ ቁጥር 587/2000 መሰረት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይባል እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ከ2010 ዓ/ም አጋማሽ ጀምሮ በሀገሪቱ በተጀመረው የፖሊቲካና የኢኮኖሚ ለውጥ ምክንያት ተቋማትና አደረጃጀታቸውን እንደገና መከለስ በማስፈለጉ ቀድሞ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የነበረው መስሪያ ቤት እንዲለያይ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የሀገር ውስጥ ገቢዎች በተመለከተ የሚወጡ ሕጎችን እንዲያስፈጽም የገቢዎች ሚኒስቴር በ2011 ዓ/ም ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሆኖ እንዲደራጅ ሲደረግ በቀድሞ ሕግ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በደምሳሳው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላለፉ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡[4] ይህ ማለት በታክስ እና ጉምሩክ ሕጎች መመሪያ ስለማውጣት የተደነገጉ ህጎችንም የሚያስፈጽመው የገቢዎች ሚኒስቴር ነው ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በተጨማሪም የጉምሩክ ኮሚሽንን ተግባር፣ ኃላፊነትና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 437/2011 የገቢዎች ሚኒስቴር ይህንን ደንብ የሚያስፈጽም መመሪያ ሊያውጣ እንደሚችል ያመለክታል፡፡[5]

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንድ ላይ ተጣምሮ ሲታይ ከላይ ከተመለከትነው መመሪያ የማውጣት ስልጣን ሙሉ ለሙሉ ለገቢዎች ሚኒስቴር ከሰጠው ጋር የማይጣጣም ድንጋጌ ይዟል፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 859/2006 የትርጉም ክፍል አንቀጽ 55 መሰረት ባለስልጣን ማለት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማለት እንደሆነ ይተረጉማል፡፡ በመሆኑም በዚህ አዋጅ መሰረት ባለስልጣኑ መመሪያ ያወጣል የሚል ድንጋጌ ካለ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እንደሆነ ከትርጉም ክፍሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ከላይ እንደተመለከትነው መመሪያ የማውጣት ስልጣን የገቢዎች ሚኒስቴር

[4] የፌዴራል ስራ አስፈጻሚዎች ተግባርና ኃላፊነት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 31

[5] የጉምሩክ ኮሚሽን ተግባር፣ ኃላፊነትና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣው የሚኒስቴሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 437/2011 አንቀጽ 12

እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጉምሩክ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 2(1) በአዋጅ ቁጥር 859/2006 በአንቀጽ 2 ንኡስ ቁጥር 55 ላይ ባለስልጣን ማለት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እንደሆነ የተሰጠውን ትርጉም በመተካት ኮሚሽን ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን ማለት እንደሆነ ይተረጉማል፡፡ በዚህ ማሻሻያ ትርጉም መሰረት ለጉምሩክ አዋጅ አፈጻጸም በአዋጅ ቁጥር 859/2006 የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚለው በጉምሩክ ኮሚሽን ተተክቶ ሲነበብ በአዋጁ ለባለስልጣኑ(የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን) የተሰጠው መመሪያ የማውጣት ስልጣን ለጉምሩክ ኮሚሽን ተሰጥቷል የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ በቅርቡ የወጣው የፌዴራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 በሌሎች ሕጎች የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢንና ታክስን በተመለከተ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል በማለት በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 1097/2011 በጥቅሉ ለገቢዎች ሚኒስቴር ከተሰጠበት አካሄድ የተለየ አቋም ወስዷል፡፡ ከዚህ አንጻር የጉምሩክ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል ሀሳብ እንዳለና ይህን ያልጠሩ መሰል ጉዳዮች የማረም ስራ ሊኖር እንደሚችል ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

የሆነው ሆኖ የጉምሩክ ኮሚሽንና የገቢዎች ሚኒስቴር ሁለት ራሳቸውን የቻሉ የአስተዳደር ተቋማት ቢሆኑም አሁን ባለው አሰራር መሰረት የጉምሩክ ሕጎችን መሰረት ያደረጉ መመሪያዎችን አጽድቆ ስራ ላይ የማዋል የገቢዎች ሚኒስቴር ስልጣን ነው፡፡

በመሆኑም በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ላይ የመመሪያ አወጣጥ ሂደት መርሆዎችን ማክበር መፈጸምና ማስፈጸም በዋናነት የገቢዎች ሚኒስቴር ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የጉምሩክ ኮሚሽን ድርሻ እንደ አንድ በገቢዎች ሚነስቴር የሚገኝ የስራ ክፍል ረቂቅ መመሪያ አዘጋጅቶ ወደ ገቢዎች ሚኒስቴር መላክ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር መመሪያ የማውጣትና የማስመዝገብ አፈጻጸም በሚመለከት በሕግና በአሰራር ለገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠ ኃላፊነት በመሆኑ በዚህ ረገድ ያለው አፈጻጸም በገቢዎች ሚኒስቴር በተደረገው የክትትል ሪፖርት ላይ ስለተካተተ የጉምሩክ ኮሚሽን ከመመሪያ አወጣጥ አንጻር ያለው አፈጻጸም በዚህ ሪፖርት ሳይካተት ቀርቷል፡፡

በሌላ በኩል ኮሚሽን መስሪያ ቤቱ የወጪ ንግድ ቀረጥና ታክስ አሰባሰብ በተመለከተ የሚወጡ ሕጎችን እንዲያስፈጽም በዚያው ዓመት በሚኒስቴሮች ምክር ቤት እንዲቋቋም ተደርጎ[6] ተጠሪነቱ ለገቢዎች ሚኒስቴር እንዲሆን ተወስኗል፡፡[7] የጉምሩክ ኮሚሽን የሚያስፈጽማቸው የቀረጥና ታክስ ሕጎች ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል የግብር አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
- የተ.እ.ታ. አዋጅ ቁጥር 285/94፣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001፣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1157/2011
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008፣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012
- የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 89/95
- የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004
- ወደሀገር ውስጥ ለሚገቡ እቃዎች የተጣለ ተጨማሪ ቀረጥ ደንብ ቁጥር 133/99
- የጉምሩክ ኮሚሽን ተግባር፣ ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 437/2011 ከተዳሰሱት መካከል ናቸው፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን ተግባር፣ ኃላፊነትና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣው የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ[8] ላይ ኮሚሽኑ በኮሚሽነሩ በበላይነት የሚመራ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች እና ሌሎች አስፈላጊ አደረጃጀቶች እንደሚኖሩት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በኮሚሽነሩ ስር ሶስት ዘርፍ እንዲኖረው የተደረገ ሲሆን በምክትል ኮሚሽነሮች የሚመሩ ናቸው፡፡ እነርሱም፦

- የጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ፣
- የጉምሩክ ሕግ ተገዢነት ዘርፍ እና
- ተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ ናቸው፡፡

---

[6] የጉምሩክ ኮሚሽን መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 437/2011

[7] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 33(21) እና አሁን ስራ ላይ ያለው የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 83

[8] ደንብ ቁጥር 437/2011 አንቀጽ 4

በአጠቃላይ በዋና መስሪያ ቤት 15 ዳይሬክሬቶች ያሉ ሲሆን ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር ይበልጥ ቁርኝት ያላቸውን የስራ ክፍሎች መርጠናል። የጉምሩክ ኮሚሽን ከዋናው መስሪያ ቤት በተጨማሪ የሚከተሉት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አሉት።

- አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- አዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ሃዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- አዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ጅቡቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- መቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ድሬደዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት

የተቋቋመበት ዓላማ በዝርዝር አስቀምጧል። ይህም በደንቡ አንቀጽ 4 ስር የተገለጹት ናቸው። እነርሱም፦

- ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
- ወደሀገር በሚገቡና ወደውጭ ሀገር በሚላኩ ዕቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ በወቅቱና በብቃት መሰብሰብ፣
- አግባብነት ያላቸውን የጉምሩክ ሕጎችና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ያጸደቀቻቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
- ወደሀገር እንዳይገቡና ከሀገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ወይም ስለአገባባቸውና አወጣጣቸው ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች መቆጣጠር፣

- የጉምሩክ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን መከላከልና መቆጣጠር የሚሉት ናቸው፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካት ደግሞ ኮሚሽኑ የሚከተሉትን ተግባር እንደሚያከናውን በደንቡ አንቀጽ 5 ላይ ተዘርዝሯል፡፡ ይህም፦

- የቀረጥና የታክስ ማስከፈያ ዋጋ መተመን፣
- በሕግ መሰረት ቀረጥና ታክስ እንዲሁም የፈቃድና የአገልግሎት ክፍያ መሰበሰብ፣
- የጉምሩክ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የአስመጪዎች፣ የላኪዎች ወይም በማንኛውም ሰው ይዞታ ስር የሚገኙ ሰነዶችን መመርመር፣
- በጉምሩክ ወደቦችና በወሰን አከባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ ጣቢያዎች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችና መጓጓዣዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞባቸው ስለመግባታቸው መፈተሽ፣
- በጉምሩክ ሕጎች መሰረት ልዩ ልዩ ፈቃዶችን መስጠት ወይም ማደስ ወይም ማገድ ወይም መሰረዝ፣
- ለጉምሩክ ስራ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችንና ጽሁፎችን ማዘጋጀት የሚሉት ከተግባራቱ መካከል ዋናዎቹ ናቸው፡፡

2.2 የጉምሩክ ኮሚሽን አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

በጉምሩክ ኮሚሽን የአስተዳደራዊ ውሳኔ መስጠት የሚጀምረው በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ባለሙያ ወይም የስራ ሂደቶች አማካኝነት ነው፡፡ በእዚህ ደረጃ ላይ ለሚሰጡ ውሳኔዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎች በመጀመሪያ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳይ አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል ቀርበው እንዲታዩ ይደረጋል፡፡ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል በወሰነው ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች ደግሞ በዋና መስሪያ ቤት ላለው የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል ቀርበው በድጋሚ ታይተው እንዲወሰኑ ይደረጋል፡፡ በዋና መስሪያ ቤት ያለው የአቤቱታ አጣሪ የውርስና የአስተዳደራዊ ቅጣት ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በተመለከተ በቀጥታ የማየት ስልጣን በተሰጠው መሰረት የውሳኔ ሀሳብ ለኮሚሽነሩ ወይም ለተወካዩ የሚያቀርብ ሲሆን የቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ አጣሪ በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ደግሞ በራሱ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

2.2.1 የአቤቱታ ወይም ቅሬታ ማቅረቢያ መንገዶች

የአቤቱታ ወይም የቅሬታ አቀራረብን መሰረት በማድረግ በሁለት መንገድ ሊከፈል ይችላል፡፡ እነርሱም በአካል የሚቀርብ አቤቱታና በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የሚቀርብ አቤቱታ ናቸው፡፡

ሀ) በአካል የሚቀርብ አቤቱታ

በአካል የሚቀርብ አቤቱታ ማለት ተገልጋዩ ወደ ጉምሩክ መስሪያ ቤት በአካል በመገኘት በቃል ወይም በጽሁፍ የሚያቀርበው አቤቱታ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን የወጣው መመሪያ በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የማይቀርቡ የዲክላራሲዮን ዓይነት በመዘርዘር አቅራቢው በቃል ብቻ ዲክላራሲዮን ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡[9]

ለ) በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚቀርብ አቤቱታ

በጉምሩክ ኮሚሽን ተግባራዊ የተደረጉ ሁለት ዓይነት የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት መስጫ ስርዓቶች አሉ፡፡ እነርሱም የኢትዮጵያ ጉምሩክ መረጃ ስርዓት (Ethiopian Customs Management System) እና የቀረጥና ታክስ ትመና ስርዓት (Ethiopian Customs Valuation System) ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ጉምሩክ መረጃ ስርዓት (ECMS) የሚባለው አስመጪው ወይም ላኪው በአካል መቅረብ ሳይጠበቅበት ከጉምሩክ ባለሙያና የስራ ሂደቶች ጋር ዲክላራሲዮን የሚያቀርብበት፣ የቀረጥና ታክስ ማስታወቅያ ማቅረብ የሚችልበት፣ የሰነዶች ፍተሻና ማረጋገጫ በተመለከተ የሚሰጡ ውሳኔዎች መረጃ የሚለዋወጡበት ስርዓት ነው፡፡ በሌላ በኩል የቀረጥና ታክስ ተመን የመረጃ ቋት (ECVS) ደግሞ የጉምሩክ ባለሙያ አስመጪው ወይም ላኪው ያቀረበው የቀረጥና ታክስ መጠን ባግባቡ አይደለም ብሎ ሲያምን ኮሚሽኑ ባዘጋጀው የመረጃ ቋት በማነጻጸር ዋጋ ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ ተገልጋዩ ተመዝግቦ የራሱ የመለያ ስምና የይለፍ ቃል እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ ተገልጋዩ በተሰጠው መለያ ስምና የይለፍ ቃል መሰረት ወደ ኦንላይን ስርዓቱ በመግባት አገልግሎት ወደፈለገበት የስራ ሂደት አቤቱታውን ያቀርባል፡፡

---

[9] የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 118/2008 አንቀጽ 4፣ 5

2.2.2 የአስተዳደራዊ ውሳኔ ዓይነቶች

በአጠቃላይ የጉምሩክ ኮሚሽን የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ ይህም፦

ሀ) የቀረጥና ታክስ ውሳኔ እና

ለ) ከቀረጥና ታክስ ውጪ ያሉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ናቸው፡፡

ሀ. ከቀረጥና ታክስ ጋር ተያያዥ የሆኑ ወሳኔዎች

i. የቀረጥና ታክስ ዕዳዎች ላይ የሚሰጥ ውሳኔ

የቀረጥና ታክስ ውሳኔ አሰጣጥ በተመለከተ የጉምሩክ አዋጅ ላይ ተመልክቷል፡፡[10] በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 87 ላይ የቀረጥና ታክስ ዕዳዎችን አስመጪው ወይም ላኪው የንግድ መዝገቦችን ተጠቅሞ በራሱ እንዲተምን ኮሚሽኑ ሊፈቅድ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ለማስፈጸም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 158/2011 ከዋጋ አተማመን ጋር በተያያዘ ዝርዝር ጉዳዮችን ይዟል፡፡ በዚሁ መሰረት በመርህ ደረጃ አሁን በጉምሩክ ኮሚሽን ያለው አሰራር አስመጪው ወይም ላኪው የዕቃውን ቀረጥና ታክስ በራሱ ተምኖ እንዲያቀረብ የሚፈቅድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጉምሩክ ባለሙያው የቀረበው የዕቃ ዋጋ ተመን በሕጉ መሰረት ያልቀረበ ከሆነና ዋጋው አጠራጣሪ ሲሆን[11] የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት (Ethiopian Customs Valuation System) ላይ ባለው የዋጋ ማነጻጸሪያ ቋት መሰረት የዕቃውን ዋጋ በመወሰን ያሳውቀዋል፡፡[12]

ii. ዲክላራሲዮን ስለመቀበል ወይም አለመቀበል የሚሰጥ ውሳኔ

የጉምሩክ አዋጅ ማንኛውም ወደ ሀገር የሚገባ ወይም ከሀገር የሚወጣ ዕቃ ዲክላራሲዮን ሊቀርብበት እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡[13] አዋጁ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ በተመለከተ በሚደነግገው ርዕስ ስር ዲክላራሲዮን በቃል፣ በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ሊቀርብ

---

[10] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008

[11] የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 158/2011 አንቀጽ 5(2)

[12] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀጽ 99፣ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 158/2011 አንቀጽ 5(3)

[13] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀጽ 12

እንደሚችል ተመልክቷል፡፡[14] በቃል ወይም በአካል እንቅስቃሴ የሚቀርብ ዲክላራሲዮን ማለት መንገደኛው ቀረጥና ታክስ የማይከፈልበት ዕቃ ከያዘ በአረንጓዴ ማለፍያ በኩል የሚያልፍ ሲሆን ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ከያዘ ደግሞ በቀይ ማለፍያ በኩል በማለፍ በአካል እንቅስቃሴ ዲክላራሲዮን እንዳቀረበ እንደሚቆጠር የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም መመሪያ ላይ ተመልክቷል፡፡[15] እንዲሁም መንገደኛው ስለያዛቸው ዕቃዎች ለጉምሩክ ኦፊሰር ቀርቦ በቃል መግለጫ ሲሰጥ በቃል የቀረበ ዲክላራሲዮን እንዳቀረበ እንደሚቆጠር በዚሁ መመሪያ ላይ ተገልጿል፡፡ በጽሁፍ የሚቀርብ ዲኪላራሲዮን ሲሆን የማጓጓዣ ሰነድ፣ የዋጋ ሰነድ፣ የባንክ ፈቃድ፣ የዕቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፣ የስሪት አገር የምስክር ወረቀት እና ሌሎች ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ ደጋፊ ሰነዶች በአባሪነት መቅረብ እንደሚገባቸው ተደንግጓል፡፡[16] የዕቃ ዲክላራሲዮን ከቀረበ በኋላ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ወዲያውኑ ውሳኔውን በጽሁፍ በመስጠት ለባለጉዳዩ ማሳወቅ እንደሚገባ በጉምሩክ አዋጁ ላይ ተመልክቷል፡፡[17]

iii. ዲክላራሲዮን እንዲሻሻል ወይም እንዲሰረዝ የሚሰጥ ውሳኔ

አስቀድሞ ለኮሚሽኑ የቀረበ ዲክላራሲዮን ከተዘረዘሩት እንዲሻሻል ወይም እነዲሰረዝ የመጠየቅ መብት ለዲክላራሲዮን አቅራቢው በጉምሩክ አዋጁ ተፈቅዶለታል፡፡[18] በዚሁ መሰረት የቀረበ አቤቱታ ላይ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ዲክላራሲዮኑ እንዲሻሻል ወይም አይሻሻልም የሚል ውሳኔ ይሰጣል፡፡[19] በሌላ በኩል ኮሚሽኑ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ ለመሰብሰብ እና በወጪ ዕቃዎች ላይ የተገኙ ልዩነቶችን ለማስተካከል ዲክላራሲዮን እንዲሻሻል ማድረግ እንደሚችል በመመሪያው ተመልክቷል፡፡[20] ዲክላራሲዮን እንዲሰረዝ ማድረግን በተመለከተ ደግሞ አቅራቢው ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቅያ ከተዘጋጀበት ቀን በኋላ ባሉት አምስት የስራ ቀናት ውስጥ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ካልጀመረ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ማድረግ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ ላይ ተገልጿል፡፡[21] አቤቱታው የቀረበለት የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት ዲክላራሲዮን የመሰረዝ ወይም

[14] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 9
[15] የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር118/2008 አንቀጽ 11
[16] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀጽ 10
[17] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 13(2)፣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር118/2008 አንቀጽ 16(3)(4)
[18] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀጽ 14፣ 15
[19] የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር118/2008 አንቀጽ 17(4)
[20] የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር118/2008 አንቀጽ 17(6)
[21] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 15(1)

አለመሰረዝ ውሳኔ በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡[22]

iv. የአስተዳደራዊ ቅጣት ውሳኔ

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 148 መሰረት ኮሚሽኑ የጉምሩክ ጥፋቶች በፈጸሙ ግለሰቦች ላይ ሕጉ በሚያዘው መሰረት የገንዘብ መቀጮ የመጣልና የማስፈጸም ስልጣን እንደሚኖረው ተመልክቷል፡፡ እንደጉዳዩ ዓይነት መቀጮውን የሚጥሉት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የስራ ሂደትና የሕግ ማስከበር የስራ ሂደት አማካኝነት እንደሆነ የጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣትና የዕቃ ውርስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 112/2008 ላይ ተገልጿል፡፡[23] የአስተዳደራዊ ቅጣት ውሳኔ ማጓጓዣዎችንና የዕቃዎችን ውርስ ይጨምራል፡፡[24]

v. ስለ ድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲትና በልዩነት ስለሚፈለግ ቀረጥና ታክስ

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን አጠናቀው የተለቀቁ ዕቃዎችን ዲክላራሲዮን የድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዲክላራሲዮኑ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ኮሚሽኑ ኦዲት ሊያድርግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡[25] ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክነያት ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት እንደሆነ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈል እንደሚችል በሕጉ ላይ ተመላክቷል፡፡[26]

ለ) ከቀረጥና ታክስ ውጪ ያሉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች አሰራር

በእነዚህ አገልግሎት አሰጣጥ ቅር የተሰኘ ተገልጋይ ቅሬታ የሚያቀርብበት ስርዓት በቅሬታ ማስተናገጃ መመሪያ ቁጥር 129/2010 መሰረት የሚመራ ነው፡፡ ከታክስና ቀረጥ ውሳኔ ውጪ በሚነሱ የአስተዳደራዊ ውሳኔ ወይም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው እርከኑን ጠብቆ እስከ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ድረስ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል በመመሪያው ተመላክቷል፡፡ በዚህም መሰረት የጉምሩክ ባለሙያ በወሰነው ቅሬታ ያለው ለቡድን መሪ

---

[22] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 22(ሠ)(ረ)
[23] የጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣትና የዕቃ ውርስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 112/2008 አንቀጽ 14(1)(2)
[24] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 147፣ የጉምሩክ ጥፋቶች አስተዳደራዊ ቅጣትና የዕቃ ውርስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 112/2008 አንቀጽ 15
[25] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 121(4)
[26] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 122(1)

እንደሚያቀርብ ከዚያም ለስራ ሂደት እያለ እስከ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ድረስ መቅረብ እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ በሚሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ባለጉዳይ ወደ ዋና መስሪያ ቤት ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚችል ይኸው መመሪያ ይፈቅዳል፡፡

ክፍል ሶስት

3. የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት

3.1 የቀረጥና ታክስ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ

3.1.1 አቤቱታ አቀራረብ

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ 1183/2012 የአስተዳደር ውሳኔ የሚቀርብበትን አኳኋን ከአንቀጽ 20 እስከ 22 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህም ሶስት ዋና ወና ጉዳዮችን በውስጡ ይዟል፡፡

- የመጀመሪያው የአስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጠኝ የሚለው ሰው ማንነት ነው፡፡ ይህም አስቀድሞ መብቱ ወይም ጥቅሙ የተነካበት አሊያም የአስተዳደር ውሳኔው ይሰጠኝ ጥያቄ ባያቀርብም በመብቱ ላይ ጉዳት ሊደርስበት የሚችል ሰው በራሱ ወይም በወኪሉ መቅረብ እንደሚገባው የሚደነግገው ነው፡፡[27]
- ሁለተኛው ከአስተዳደር ተቋሙ ባህሪ የተነሳ ምንም እንኳ አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው ባይኖርም በራሱ አነሳሽነት ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ ነው፡፡[28] ከዚህ አንጻር የገቢዎች ሚኒስቴር አፈጻጸም ተመልክተናል፡፡
    - አዎንታዊ እርምጃ
        - ተገልጋይ አቤቱታ ሲያቀርብ የሚሰጥ ውሳኔ መኖሩ (ምሳሌ፦ በራሱ የዋጋ ተመን በማቅረብ ቀረጥ ና ታክስ እንዲወሰንለት አስመጪው ወይም ላኪው የሚጠይቅበት)
        - ተቋሙ በራሱ አነሳሽነት የሚሰጠው ውሳኔ መኖሩ (ምሳሌ፦ ኮሚሽኑ የስጋት ደረጃቸው በመለየት የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በማድረግ የሚወሰን ቀረጥና ታክስ)
        - የአቤቱታው አቅራቢ የሚመለከተው ስለመሆኑ የማረጋገጥ አሰራር ተዘርግቷል፡፡ ለምሳሌ የንግድ ፈቃድ፣ መታወቅያ…ማስቀረብ
    - አሉታዊ ጎን
        - የለም

---

[27] የአስተዳደር ሥ/ሥ/አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 20(1)

[28] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 20(2)

3.1.2 አቤቱታ በጽሁፍ እንዲቀርብ ከማድረግ አንጻር

ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ ይሰጠኝ የሚል አካል ጥያቄውን በጽሁፍ ማቅረብ እንዳለበት በአዋጁ ላይ ተደንግጓል።[29] ከላይ እንደተገለጸው የጉምሩክ ኮሚሽን አሰራር ስንመለከት የሚቀርበው አቤቱታና የሚሰጠው ምላሽ ወይም ውሳኔ በሁለት መንገድ ነው። የመጀመሪያው ባለጉዳዩ በአካል በመቅረብና ጉዳዩን በማስረዳት የሚቀርብ አቤቱታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በኤሌክትሮኒክስ አማካኝነት ባለጉዳዩ በአካል መቅረብ ሳይጠበቅበት በኦንላይን አቤቱታ የሚያቀርብበትና ውሳኔ የሚያገኝበት ስርዓት ነው።

- አዎንታዊ እርምጃ
  - በአዋጁ መሰረት አቤቱታ በጽሁፍ የሚቀርብበት አሰራር መኖሩ፣
  - በኤሌክትሮኒክስ የሚቀርብ አቤቱታ መኖሩ፣
- አሉታዊ ጎን
  - በቃል የሚቀርብበት ሁኔታ መኖሩ፣(ምሳሌ፦ በቃል የሚቀርብ የዲክላራሲን አቤቱታ መኖሩ)
  - በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የሚሰጠው አገልግሎት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ መሆኑ፣ (የፌዴራል የስራ ቋንቋ አለማክበር)
  - በአዋጁ መሰረት አንድ አቤቱታ ሊይዝ የሚገባውን ዝርዝር ጉዳይ ማለትም ቀን፣ የአቤቱታ አቅራቢው ወይም ወኪሉ ስም፣ ፊርማ እና አድራሻ፤ አስተዳደራዊ ተግባሩን የሚፈፅመው ተቋም ስም፤ የአቤቱታ አቅራቢው መብት ወይም ጥቅም፤ ተቋሙ ሊፈፅመው የሚገባ አስተዳደራዊ ተግባር፤ ተቋሙ ለሚተገብረው አስተዳደራዊ ተግባር መሰረት የሆኑ ምክንያቶች እና ተያያዥ ማስረጃዎች በኢሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጦችን በተሟላ መንገድ አለመቅረባቸው፣ (chat box format)

i. ጉዳዩን ስለመስማት

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ስለጉዳይ መስማት በሚል ርዕስ ስር ባሉት ድንጋጌዎች ጉዳይ በሚሰማበት ጊዜ ባለጉዳዩ በክርክሮች ሂደት ሁሉ ተገኝቶ ምስክርነት የመስጠት፣

[29] የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 21

ምስክሮችን እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማቅረብ እና የማሰማት በተቋሙ የቀረቡ ማስረጃዎችን የማየትና የመመርመር መብት እንዳለው ያትታል፡፡[30] ከዚህ አንጻር የጉምሩክ ኮሚሽን አሰራር ተመልክተናል፡፡

- አዎንታዊ እርምጃ
  - በኮሚሽኑ አነሳሽነት ለሚሰጡ ውሳኔዎች ለባለጉዳዩ ማስታወቅያ የሚላክበት አሰራር መኖሩ፣ (ምሳሌ፦ የድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት)
  - ከውሳኔ በፊት ከባለጉዳዩ ጋር የመግቢያና መውጫ ውይይት መደረጉ ባለጉዳዩ ጉዳዩን እንዲያስረዳ ዕድል የሚፈጥርለት መሆኑ፣ (ምሳሌ፦ የድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት)
  - ባለጉዳዩ አቤቱታውን የሚያስረዳለት ማስረጃዎች የማቅረብ መብቶች ተግባራዊ የሚደረጉ መሆኑ፣ (ምሳሌ፦ ከዲክላራሲዮን ጋር በተያያዘ የዕቃ ዋጋ ለመተመን፣ ታሪፍ ለመመደብና ቀረጥና ታክስ ለመወሰን የሚቀርብ የሰነድ ማስረጃዎች የሚመረመሩበት አግባብ)
  - ባለጉዳዩ በአካል ቀርቦ የሚያስረዳበት አሰራር መኖሩ፣
  - የዕቃ ወይም የማጓጓዣ ውርስ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የዕቃው ባለቤት ወይም ተወካይ የሚታወቅ ሲሆን መቃወምያ ካለው እንዲያቀርብ የማይታወቅ ከሆነ ደግሞ ባለቤቱ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጭምር ጥሪ እንዲደረግለት የጉምሩክ አዋጅ የሚያዝ ሲሆን[31] ይህም በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ባላጉዳዩ በአካል ቀርቦ ጉዳዩን የማስረዳትና የመከታተል ከተፈቀደለት መብት ጋር የሚጣጣም መሆኑ፣
  - የኤሌክትሮኒክስ መንገድ የሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተገልጋዩ በአካል ወደ ጉምሩክ መስሪያ ቤት መምጣት ሳያስፈልገው ባለበት ሆኖ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል አሰራር የተገልጋዩን ምልልስ በመቀነስ ጊዜንና ሀብትን በመቆጠብ የተቀላጠፈ ውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር የሚያስችል መሆኑ (ECVS and eCMS)፣
- አሉታዊ ጎን

[30] የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 37
[31] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀጽ 143

- የኦንላይን አገልግሎት ስርዓት መቋረጥ ወይም ብልሽት (system down) በሚያደርግበት ወቅት እና የኤሌክትሪክ ኃይል መጥፋት ሲያጋጥም አገልገሎቱ ለጊዜው የሚቋረጥ በመሆኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ በወቅቱ ከመስጠት አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር መሆኑ፣
- መመሪያው የሚከለክል ባይሆንም በተጨባጭ በጉምሩክ ኮሚሽን ያለው አሰራር ግን የዲክላራሲዮን አቀራረብ የሚስተናገደው በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ብቻ እንዲሆን መደረጉ፣

3.1.4 የአስተዳደር ውሳኔ ለተገልጋዩ ስለመስጠት

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ውሳኔን ለተገልጋዩ ስለመስጠት በሚል ባስቀመጠው ድንጋጌ ላይ ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ ከነምክንያቱ ለተገልጋዩ በጽሑፍ መሰጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡[32] እንዲሁም ማንኛውም የአስተዳደራዊ ውሳኔ ቀንና ቁጥር፣ የተቋሙን ስም፣ በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፣ አከራካሪ ፍሬ ነገር፣ የማስረጃዎች ትንተና፣ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንታኔ እነዲሁም የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ መያዝ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡[33] ከዚህ አንጻር የጉምሩክ ኮሚሽን አሰራር ተመልክተናል፡፡

- አዎንታዊ እርምጃ
  - የኦንላይን አገልግሎት በተመለከተ በላጉዳዩ የሚሰጠው ውሳኔ በኤሌክትሮኒክስ መተግበሪያው አማካኝነት በቀጥታ የሚደርሰው መሆኑ፣
  - በጽሁፍ የሚሰጡ ውሳኔዎች ለተገልጋዩ እንዲሰጠው መደረጉ፣
- አሉታዊ ጎን
  - በኤሌክትሮኒክስ የሚሰጡ ውሳኔዎች ይዘት በአዋጁ የተመለከቱትን ፍሬነገሮች ማለትም የተቋሙን ስም፣ በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፣ አከራካሪ ፍሬ ነገር፣ የማስረጃዎች ትንተና፣ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንታኔ በተሟላ መልክ አለመያዝ (ምሳሌ፡-በጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች)
  - በኤሌክትሮኒክስ የሚሰጡ ውሳኔዎች በእንግሊዘኛ መሆኑ(የስራ ቋንቋ አለማክበር)፣

---

[32] የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 39

[33] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 40

3.1.5 የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ስለማቋቋም

የአስተዳደር ተቋማት የሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለመስማት የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም እና ይህንኑ ለተገልጋዮች ይፋ ማድረግ እንዳለባቸው በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ላይ ተደንግጓል፡፡[34] ከዚህ አንጻር የጉምሩክ ኮሚሽን አሰራር ተመለክተናል፡፡ ከዚህ አንጻር የጉምሩክ ኮሚሽን አሰራር ተመለክተናል፡፡ ኮሚሽኑ የሚያስፈጽመው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 152 ላይ ኮሚሽኑ የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል በዋናው መስሪያቤትና ቅርንጫፎች እንደሚያቋቁም ተመልክቷል፡፡ በዚሁ አዋጅ መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታዎች በሁለት እርከን የሚታዩ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የየቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ባለሙያ ወይም የስራ ሂደቶች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች እዛው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚገኙ የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል ቀርበው የሚወሰኑ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ አጣሪ የሰራ ክፍል በወሰነው ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች ለጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያቤት ላለው የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል ቀርበው በድጋሚ ታይተው የሚወሰኑ ናቸው፡፡[35] በዋና መስሪያ ቤት ያለው የአቤቱታ አጣሪ የውርስና የአስተዳደራዊ ቅጣት ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በተመለከተ በቀጥታ የማየት ስልጣን በተሰጠው መሰረት የውሳኔ ሀሳብ ለኮሚሽነሩ ወይም ለተወካዩ የሚያቀርብ ሲሆን[36] ከቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ አጣሪ በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ደግሞ በራሱ ውሳኔ የመስጠት ስለጣን ተሰጥቶታል፡፡[37]

- አዎንታዊ እርምጃ
    - በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት ከአዋጁ መውጣት አስቀድሞ ኮሚሽኑ የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል በዋናው መስሪያ ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያደራጀ መሆኑ፣
    - የአቤቱታ አጣሪ አደረጃጀትና የባለሙያዎች ስብጥር በሕግ የተወሰነ መሆኑ፣
    - በዋናው መስሪያ ቤት ያለው አቤቱታ አጣሪ ባግባቡ የተደራጀ መሆኑ፣
- አሉታዊ ጎን

[34] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 44
[35] የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀጽ 153(2)(ሀ)
[36] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 153(2)(ለ)(ሐ)
[37] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 153(2)(ሀ)

- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላይ
    - በመመሪያው የተቀመጠውን የባለሙያ ስብጥር አለማክበር፣(ማሳያ፦ የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መመሪያው በሚያዘው መሰረት በአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል ውስጥ አንድ የሕግ ባለሙያ እንዲካተት አለመደረጉ)
    - በመመሪያ የተቀመጠውን የስራ ክፍል አደረጃጀትና የባለሙያ ስብጥር አለማክበር (ማሳያ፦የአዳማ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የአቤቱታ አጣሪ አባላት ቁጥር መመሪያው ከሚፈቅደው በታች መሆኑና የሕግ ባለሙያ እንዲካተት አለመደረጉ)

3.1.6 ቅሬታውን ስለመመርመርና ስለመወሰን

በአስተዳደር ተቋሙ የተቋቋመ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል የቀረበውን ቅሬታ በሚገባ መመርመር እና የውሳኔ ሀሳብ ለአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ ለወከለው የሥራ ኃላፊ እንደሚያቀርብ በአዋጁ አንቀጽ 46 ላይ ተደንግጓል፡፡

የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ አጣሪዎች በሁለት መንገድ ቅሬታዎችን ተቀብለው ይሰማሉ፡፡ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት (Ethiopian Customs Management System) አማካኝነት በኦንላይን የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ደንበኛው በአካል መቅረብ ሳይጠበቅበት በኦንላይን የመረጃ ልውውጥ ውሳኔ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡ ይህ አሰራር የደንበኛውንና የተቋሙን ጊዜ በመቆጠብ የተቀላጠፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ያግዛል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ የኦንላይን ስርዓት የሚሰጠው ውሳኔ በእንግሊዘኛ በመሆኑ የፌዴራል የስራ ቋንቋ ያከበረ አይደለም፡፡ ይህም በተደራጀና ግልጽ በሆነ ሁኔታ አቤቱታ ከማቅረብና ከማስረዳት አንጻር እንዲሁም ውሳኔውን በተብራራ ሁኔታ ከመተንተንና ከመጻፍ አንጻር የራሱ ውስንነት እንዳለበት ተገንዝበናል፡፡ በኦንላይን ስርዓት የሚሰጠው ውሳኔ የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ላይ የተመለከተውን የውሳኔ ይዘት አንጻር ሲታይም የተሟላ አለመሆኑን ከወሰድነው የውሳኔ ናሙና አይተናል፡፡ አገልግሎትን በኦንላይን መስጠት የሚነቀፍ ባይሆንም የሀገር ውስጥ ቋንቋዎችን ከመጠቀም ጀምሮ እያንዳንዱ ዝርዝር የአቤቱታ አቀራረብ እና የተሟላ የውሳኔ መስጫ ቅጽ እንዲኖረው ስርዓቱን ይበልጥ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ የሚደረገውም ማሻሻል በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ የተደነገጉ የውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎችን እንዲያካትት መታሰብ አለበት፡፡

ሁለተኛው የቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን በጽሁፍ አድርጎ በአካል ለአቤቱታ አጣሪ የሚያቀርብበት ስርዓት ነው፡፡ ይህ የተቋሙ ነባር አሰራር ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና የሚሰጡ ውሳኔዎች የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ላይ የተቀመጡ የውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎችን ጋር የሚጣጣምና የተሸለ አሰራር መሆንን ተገንዝበናል፡፡ በኦንላይን ከሚሰጠው አገልግሎት በተቃራኒ በጽሁፍ የሚቀርብ ቅሬታና በዚሁ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በፌዴራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ ከመሆኑም በላይ ውሳኔዎቹ በጣም በግልጽና ዝርዝር በሆነ አኳኋን የሚሰጡ ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር በዋናው መስሪያ ቤት ያለው አቤቱታ አጣሪ ባግባቡ የተደራጀ ሲሆን በተመለከትናቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ውስጥ የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የአቤቱታ አጣሪ አባላት ቁጥራቸው የተሟላ ሲሆን መመሪያው በሚያዘው መሰረት አንድ የሕግ ባለሙያ እንዲካተት አልተደረግም፡፡ የአዳማ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ላይ ደግሞ የአቤቱታ አጣሪ አባላት ቁጥር መመሪያው ከሚፈቅደው በታች ሲሆን እዚህም የሕግ ባለሙያ እንዲካተት አልተደረገም፡፡ መመሪያው ይህን የአቤቱታ አጣሪ አባላት አደረጃጀትና የባለሙያ ስብጥር ያስቀመጠበት ምክንያት የጉምሩክ ጉዳይ ውስብስብና ቴክኒካል ጉዳዮችን የያዘ በመሆኑ ጉዳዩን በሚገባ በመመርመር በቂ አስተያይትና ሀሳብ በመስጠት ውሳኔው ፍትሃዊና ትክክለኛ እንዲሆን፣ የህዝብና የመንግስት ጥቅም እንዳይጎዳ እና ደንበኞችም እንዳይጉላሉ ታስቦ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ የአቤቱታ አጣሪ አደረጃጀትና የባለሙያ ስብጥር ያልተሟላ ከሆነ የሚሰጠው ውሳኔ ትክክለኛነትና ፍትሃዊነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የታየው ክፍተት አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ክፍተት እንዳይፈጥር ከወዲሁ በመመሪያው መሰረት አደረጃጀቱንና የባለሙያ ስብጥሩን ማስተካከል ተገቢ ነው፡፡

- አዎንታዊ እርምጃ
  - ባለጉዳዮች ቅሬታ የሚያቀርቡበት ስርዓት የተዘረጋ መሆኑ፣
  - በጽሁፍ የሚቀርብ ቅሬታና በዚሁ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በፌዴራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ ከመሆኑም በላይ ውሳኔዎቹ በጣም በግልጽና ዝርዝር በሆነ አኳኋን የሚሰጡ ናቸው፡፡
- አሉታዊ ጎን
  - በኦንላይን የሚደረገው የቅሬታ መስማት ሂደት በእንግሊዘኛ ብቻ በመሆኑ የፌዴራል የስራ ቋንቋ አለማክበር፣

- ○ በአጠቃላይ በኦንላይን ስርዓት አማካኝነት የሚደረግ የቅሬታ አሰማምና ውሳኔ አሰጣጥ በአዋጁ ላይ ከተመለከተው የውሳኔ ይዘት አንጻር ሲታይም የተሟላ አለመሆኑን ከወሰድነው የውሳኔ ናሙና አይተናል፡፡

3.1.7 ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለማሳወቅ

በአዋጁ አንቀጽ 47 ላይ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም በቀረበው ቅሬታ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ወዲያውኑ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚህ ረገድ የጉምሩክ ኮሚሽን አሰራር ስንመለከት በኦንላይን የተሰጠ ውሳኔ ይሁን በጽሁፍ ቅሬታውን ላቀረበው ሰው እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

- ➢ አዎንታዊ እርምጃ
  - ○ ውሳኔው በኦንላይን አማካኝነት ወይም በአካል ለባለጉዳዩ የሚሰጥ መሆኑ፣
- ➢ አሉታዊ ጎን
  - ○ በሲስተም ችግር ምክነያት ውሳኔ ሳይሰጥ ሊዘገይ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ፣

3.2 ከታክስ ውጪ ያሉ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ

ከታክስና ቀረጥ ውሳኔ ውጪ በሚነሱ የአስተዳደራዊ ውሳኔ ወይም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለሚሰጡ አገልግሎት እርከኑን ጠብቆ እስከ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ድረስ አቤቱታ የሚያቀርብበት ሥርዓት በተገልጋዮች ቅሬታ ማስተናገጃ መመሪያ ቁጥር 129/2010 መሰረት የሚመራ ነው፡፡

- ➢ አዎንታዊ እርምጃ
  - ○ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት በመመሪያ የተዘረጋ መሆኑ፣
  - ○ አቤቱታ ወይም ቅሬታው በኢሜይል ወይም በተጻፈ ማመልከቻ የሚቀርብበት ሁኔታ መኖሩ፣
  - ○ በጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት ከቀረጥና ታክስ ውጪ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንና የተሰጡ ውሳኔዎችን ሰነዶ ከመያዝ አንጻር የተሸለ መሆኑ፣
  - ○ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ ተቀብሎ በመስማት ውሳኔ የመስጠትና በኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊ ለሚሰጡ ውሳኔዎች ደግሞ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ አሰራር መኖሩ፣

- አሉታዊ ጎን
  - አቤቱታ ወይም ቅሬታ በቃልና በስልክ ማቅረብ የሚቻልበትሁ ሄኔታ መፈቀዱ አዋጁ በጽሁፍ መደረግ እንዳለበት ከሚደነግገው ጋር የማይጣጣም መሆኑ፣
  - ከታክስና ቀረጥ ጉዳዮች ውጪ የሆኑ አስተዳደራዊ አገልግሎቶች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች አቤቱታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ወጥ አለመሆኑ
  - በዚህ መንገድ ለቀረበው አቤቱታ በተመሳሳይ መንገድ ምላሽ የሚሰጥ መሆኑ፣
  - በእነዚህ ጉዳይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና የሚሰጡ ውሳኔዎችን በተደራጀ ሁኔታ ሰንዶ ያለመያዝ ክፍተት የሚስተዋል መሆኑ (በተለይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላይ የቀረበ አቤቱታ ወይም የተሰጠ ውሳኔ ናሙና ማግኘት አለመኖር)፣

3.3 ስለአዋጁ ግንዛቤ በተመለከተ

የአስተዳደር ተቋማት በአዋጁ ላይ የተቀመጡ መርሆዎችን አክብሮ ለመፈጸም ለስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስለአዋጁ ግንዛቤ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የጥናት ቡድኑ ጉምሩክ ኮሚሽን በመሄድ መረጃ ከሰበሰበባቸው ጉዳዩች አንዱ የአዋጁን ግንዛቤ በተመለከተ ነው፡፡ በተደረገው የቡድን ውይይትና ቃለመጠይቅ መረጃ መሰረት ኮሚሽኑ ለስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞቹ በስልጠናም ይሁን በሰርኩላር ስለአዋጁ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ የተሰራ ስራ አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በግል ጥረት ጥቂት የተቋሙ ሰራተኞች ስለአዋጁ ግንዛቤ እንዳላቸው ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ ስለአዋጁ አስፈላጊነትና ይዘት ግንዛቤ መፍጠር ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

ከግንዛቤ ጋር የተያያዘው ሌላው ነገር የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁን መርሆዎች እንዴትና በማን ተግባራዊ መደረግ አለባቸው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ የክትትል ቡድኑ መረጃ ለመሰብሰብ ወደተቋሙ በሄደበት ወቅት በአዋጁ የተቀመጡ የመመሪያ አወጣጥ ሂደቶችና የውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን የሚከታተል አካል የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከመመሪያ ማውጣት ጋር በተያያዘ ግን በኮሚሽኑ የውስጥ አደረጃጀት ሰነድ መሰረት የሕግ አገልግሎት ክፍል ከሚመለከተው ቴክኒካል የስራ ክፍል በሚቀርበው መነሻ መሰረት ረቂቅ መመሪያዎችን የማዘጋጀት፣ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና የበላይ አመራሩ አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ እና የመጨረሻውን ረቂቅ ለሚኒስትሩ አቅርቦ የማጸደቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም የመመሪያ አወጣጥ በሚመለከት አሁንም ድረስ ተግባራዊ እየተደረገ

ያለው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ያለው ነባሩ አሰራር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሁሉም የስራ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ሲወጡ በአዋጁ የተቀመጡ መርሆዎችን ታሳቢ አድርገው እንዲፈጽሙ የስራ መመሪያ መስጠት ወይም ይህንን ጉዳይ እንዲያስተባብር ለአንድ የስራ ክፍል መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ክፍል አራት

4. ማጠቃለያና ምክረ ሀሳብ

4.1 ማጠቃለያ

የጉምሩክ ኮሚሽን ከአዋጁ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ መመሪያ ስለማውጣትና አስተዳደራዊ ውሳኔ ስለመስጠት የተመለከቱት ጉዳዮች አፈጻጸም በጥናቱ ላይ ተመልክቷል፡፡ ከመመሪያ አወጣጥ ሂደት ከመከተል ጋር በተያያዘ ኮሚሽኑ የሚያስፈጽማቸውን መመሪያዎች የሚያወጣው የገቢዎች ሚኒስቴር ነው፡፡ በዚህ ረገድ በአሰራር የጉምሩክ ኮሚሽን ድርሻ ረቂቅ መመሪያ የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ እና ገቢዎች ሚኒስቴር ደግሞ የማጽደቅ ስልጣን በሕግ የተሰጠው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ምክኒያት ኮሚሽኑ የመመሪያ አወጣጥ ሂደት እና ህጋዊነት አፈጻጸም ሳይዳሰስ ቀርቷል፡፡

ከአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ከአጠቃላይ የውሳኔዎቹ ባህሪ በመነሳት በኮሚሽኑ ሁለት ዓይነት ውሳኔዎች እንደሚሰጡ ተገንዝበናል፡፡ እነርሱም፦

- የቀረጥና ታክስ ጉዳዮች ውሳኔ እና
- ከቀረጥና ታክስ ውጪ ያሉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ናቸው፡፡

የቀረጥና ታክስ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ ስንመለከት አቤቱታ አቀራረብና ውሳኔ በጽሁፍ የሚደረግ መሆኑ፣ ባለጉዳዩ አቤቱታውን እንዲያስረዳ ማስረጃ የሚያቀርብበት አሰራር የተዘረጋ መሆኑ፣ የተደረሰበት ውሳኔ ለባለጉዳዩ በጽሁፍ እንዲደርሰው መደረጉ፣ ቅሬታ ተቀብሎ ከማስተናገድ አንጻር የተደራጀ የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል አደረጃጀት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ዋና መስሪያ ቤት መኖሩ፣ በቅሬታዎች ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች በጽሁፍ ተደረጎ ለባለጉዳዩ የሚሰጥበት አሰራር ተግባራዊ እየተደረገ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ከአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ መርሆዎች ጋር የሚጣጣም በመሆኑ በአዎንታዊነት የታዩ አፈጻጸሞች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል አደረጃጀት እና የባለሙያዎች ስብጥር መመሪያው በሚያዘው መሰረት ያለመፈጸም ክፍተቶች የተስተዋሉ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ መረጃ ስርዓት (Ethiopian Customs Management System) እና የቀረጥና ታክስ ትመና ስርዓት (Ethiopian Customs Valuation System) የኦንላይን ስርዓቶች የፌዴራል የስራ ቋንቋ መቀበል አለመቻላቸው እና በዚህ ስርዓት የሚቀርቡ

አቤቱታዎችና የሚሰጡ ውሳኔዎች አዋጁ በሚያዘው መሰረት ዝርዝር ጉዳዮችን እንዲይዝ ተደርጎ አለመዘጋጀቱ በአሉታዊነት የታየ አፈጻጸም ነው፡፡

ከቀረጥና ታክስ ጉዳዮች ውጪ የሆኑ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ማለት ከጉምሩክ ባለሙያ አንስቶ በየእርከኑ በሚገኙ የስራ ሂደቶች ከአገልግሎት አሰጣጥና ከስነ-ምግባር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በተመለከተ አቤቱታ የሚቀርብበትና ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ውሳኔዎች የሚሰጡበትና ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት አግባብ ወጥ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት የሚገኘው የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት አቤቱታዎችን በጽሁፍ እንዲቀርቡ ከማድረግና የሚሰጡ ውሳኔዎችን በጽሁፍ ለተገልጋዩ ከመስጠት አንጻር የተሻለ ነው፡፡ ምንም እንኳ የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽ በመመሪያ ቁጥር 129/2010 ላይ አባሪ ተደረጎ የተዘጋጀ ቢሆንም በሄድንባቸው የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በቅሬታ ማቅረቢያ ቅጹ መሰረት አቤቱታ እንዲቀርብ ከማድረግ አንጻርና በዚሁ መንገድ ከማስተናገድ አንጻር ክፍተት መኖሩን ተገንዝበናል፡፡ በተጨማሪም አቤቱታዎች በቃልና በስልክ ጭምር የሚስተናገድበት አሰራር መኖሩ ከግልጸኝነትና ወጥነት አንጻር በአሉታዊነት የሚታይ ነው፡፡

4.2 ምክረ ሀሳብ

የጉምሩክ ኮሚሽን እንደ አንድ የፌዴራል አስተዳደር ተቋም በአዋጁ የተቀመጡ የመመሪያ አወጣጥና አስተዳደራዊ ውሳኔ መርሆዎች የመተግበር ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር በጥናቱ የተገኙ ክፍተቶችን መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ከቀረጥና ታክስ በመለስ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና የሚሰጡ ውሳኔዎች በቃልና በስልክ ጭምር የሚስተናገዱ ከመሆኑ አንጻር የውሳኔ ግልጸኝነትና ተገማችነት ለማረጋገጥ አዳጋች በመሆኑ በአዋጁ ከተመለከቱት መርሆዎች በተለይ ማናቸውም አቤቱታዎችና ውሳኔዎች በጽሁፍ መሆን እንዳለባቸው ከሚያዘው ጋር የሚጣጣም አሰራር ተግባራዊ ቢደረግ፤
- በኦንላይን የሚሰጡ የታክስና ቀረጥ ጉዳዮች በተመለከተ የeCMS, ECVS ስርዓት መሰረት አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ ሲሆን ይህ ደግሞ አቤቱታውን ከማብራራት እንዲሁም የሚሰጠውን ግብረ መልስ ከመረዳት አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ከመሆኑም በላይ የፌዴራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ የመገልገል መብት ከማክበር አኳያ የማዘመን ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡
- የኦንላይን አጠቃቀም በሚመለከት በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ ማኑዋል አለ፡፡ ይህ ማኑዋል ለሁሉም ተገልጋዮች ግልጽ ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህ ማኑዋል በአማርኛ እንዲዘጋጅ ቢደረግ፤
- በጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አብዛኛው አገልግሎት በኦንላይን እንዲሰጥ እየተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህን አሰራር በሕግ ማዕቀፍ ማስደገፍ የሚያስፈግ በመሆኑ የጉምሩክ ሕጎችንና መመሪያዎች ስለኦንላይን አጠቃቀምና ስለሚያስከትለው ውጤት በተመለከተ የሕግ ማሻሻያዎች ቢደረግ፤
- አብዛኛው በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ተሳታፊ የነበሩ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስለአዋጁ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ለስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ከሁሉ የሚቀድም ተግባር ነው፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በሁለት መንገድ ማድረግ ይቻላል፡፡ የመጀመሪው ስልጠና በመስጠት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቢያንስ በሰርኩላር አዋጁን እንዲያውቁት ማድረግ ነው፡፡
- በአጠቃላይ ኮሚሽኑ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ የተቀመጡ መርሆዎች በማን እና እንዴት ተግባራዊ መደረግ አለበት የሚለውን በተመለከተ ሁሉም የስራ ክፍሎች በዕለት

ተዕለት ተግበራቸው የአዋጁን መርሆዎች ታሳቢ አድርገው እንዲፈጽሙ የስራ መመሪያ መስጠት ወይም ይህንን ጉዳይ በዋናነት እንዲያስተባብር ለአንድ የስራ ክፍል መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ዋቢ ነገሮች

ሀ. ሕጎች

1. የፌዴራል የግብር አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
2. የተ.እ.ታ. አዋጅ ቁጥር 285/94፣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001፣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1157/2011
3. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 958/2008፣ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011
4. የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012
5. የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ቁጥር 89/95
6. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004
7. ወደሀገር ውስጥ ለሚገቡ እቃዎች የተጣለ ተጨማሪ ቀረጥ ደንብ ቁጥር 133/99
8. የጉምሩክ ኮሚሽን ተግባር፣ ኃላፊነት እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 437/2011

ለ. ቃለ መጠይቅ

9. ከአቶ አሸናፊ ባሳ በጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ
10. ከአቶ ዘመኑ በጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ
11. ከወ/ሮ ስምረት በጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ
12. ከአቶ በለጠ ኮርሜ በጉምሩክ ኮሚሽን ሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/በት ኃላፊ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ
13. ከአቶ መንግስቱ በጉምሩክ ኮሚሽን የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ ጋር ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ
14. ከወ/ሮ አየሁብርሃን በጉምሩክ ኮሚሽን የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ
15. ከአቶ አቡበከር በጉምሩክ ኮሚሽን የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የንግድ ዕቃ አወጣጥ ቡድን አስተባባሪ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ

አባሪ አንድ

ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ዝርዝር ጥያቄዎች

የመንግስት አስተዳደር ተቋማት የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አተገባበርን ለመፈተሽ ለሚደረገው ጥናት ከተቋማት ባለሙያዎችና ኃላፊዎች መረጃ ለመሰብሰብ ይረዳ ዘንድ የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ;

1. የአዋጁ ግንዛቤ ላይ

   ሀ. በተቋማችሁ የፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር1183/2012 በተመለከተ ግንዛቤ የማስጨጥ ተግባር ተደርጎ ያውቃል? ማሳያዎች ያስፈልጋሉ*

   ለ. የአስተዳደር ሥነሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ከማስፈጸም አንጻር በተቋማችሁ ክትትል የሚያደርግ የስራ ክፍል ወይም ቡድን አለ?

ሀ. ከመመሪያ አወጣጥ ጋር በተያያዙ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

2. የመመሪያ ማውጫ ጊዜ

   ለ. በአ.ሥ.ሥ ሕግ አዋጅ መሰረት የመመሪያ ማውጫ የሶስት ወር ጊዜ ገደብ ቢያልፈውም እስካሁን ያልወጣ መመሪያ በተቋማችሁ አለ ? (የአ.ሥ ሥ. ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 5

3. ነባር መመሪያ ከማስመዝገብ አንጻር

   ሐ. የአ.ሥ.ሥ ሕግ ከመውጣቱ በፊት በክፍላችሁ የወጡ ምን ያህል ነባር መመሪያዎች አሉ? እነዚህ መመሪያዎች ለፍትህ ሚኒስቴር ተልከው ተመዝግበዋል ወይ? ያልተመዘገቡ ካሉ በዝርዝር ቢገለጹ; (የአ.ሥ. ሥ ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 16(4)

4. አዲስ መመሪያ የማውጣት ሂደት

   መ. ተቋማችሁ የአሰተዳደር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከወጣ በኋላ(መጋቢት 2012 ዓ/ም) አዲስ መመሪያ አውጥቷል ወይ? አዎ ከሆነ በዝርዝር ቢገለፅ;

   ሠ. ተቋማችሁ የመመሪያ አወጣጥ መዝገብ አደራጅቷል ወይ? የአ.ሥ ሥ. ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 6(1)4

የወጣ አዲስ መመሪያ ካለ ብቻ የሚመለስ

5. ተቋማችሁ የአሰተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ከወጣ በኋላ (መጋቢት 2012 ዓ/ም) አዲስ የሚወጣ ረቂቅ መመሪያን በተመለከተ ለህዝብ ተደራሽ በሆነ ጋዜጣ ወይም መገናኛ ብዙሃን ወይም በተቋማችሁ ድኅረ ገጽ አስተያየት ለመሰብሰብ የማስታወቅያ ጥሪ ተደርጓል ወይ? ካላደረገ ለምን?

6. በተቋማችሁ አዲስ የተዘጋጀ ረቂቅ መመሪያ ካለ ለባለድርሻ አካላትና ለሚመለከታቸው አስተዳደር ተቋማት አስተያየት እንስዲሰጡበት ተልኮ ያውቃል? ማሳያዎች ማቅረብ ያስፈልጋል; የአ.ሥ ሥ. ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 9(1)
7. አዲስ በተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ አስተያየት ለመሰብሰብ ተቋማችሁ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ያውቃል? ካላደረገ ለምን ?የአ.ሥ ሥ. ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 10
8. በረቂቅ መመሪያ ላይ የተሰጡትን አስተያየት መቀበል እና ማካተት በተመለከተ ተቋማችሁ ያለው አፈጻጸም ምን ይመስላል? በማሳያ መደገፍ አለበት; የአ.ሥ. ሥ ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 12(2)
9. አዲስ በሚወጣ ረቂቅ መመሪያ ላይ ተቋማችሁ የማብራሪያ ጽሁፍ ያዘጋጃል ወይ? የአ.ሥ ሥ. ሕግ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 14
10. መመሪያን ከማስመዝገብ አንጻር

    ሀ.በተቋማችሁ የወጡ አዲስ ረቂቅ መመሪያ ከነማብራሪያው ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመላክ እንዲመዘገብ ተደርገዋል ወይ?

11. መመሪያ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር

    ሀ. ተቋማችሁ የጸደቀውን መመሪያ አሳትሞ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 17(2)

    ለ.የጸደቁ መመሪያዎች በሙሉ በተቋሙ ድኅረ ገጽ ይጫናል ወይ?

    ሐ) በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቅጂ ከማዘጋጀት አንፃር

ለ.ከአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች

12. በተቋማችሁ ለተገልጋዮች የሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በዝርዝር ቢገልፁልን?
13. ተቋማችሁ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ቅጽ አዘጋጅቷል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 21(3)
14. ተቋማችሁ በአስተዳደር ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ለማስተናገድ ይቻል ዘንድ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል አቋቁሟል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 44
15. የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጠው ጥያቄ ላቀረበ ሰው ተቋማችሁ አቤቱታ መቀበሉን በተመለከተ ለአቤቱታ አቅራቢው ማረጋገጫ የሚሰጥበት አሰራር ዘርግቷል ወይ? የአ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 22
16. በተቋማችሁ አንድ የአስተዳደር ውሳኔ ለመስጠት የሚፈጀው ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የሚገልጽ አሰራር አለ ወይ? ይህ አሰራር ካለ በአማካይ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

17. በተቋማችሁ የሚሰጥ የአስተዳደር ጉዳይ ውሰኔ የመሰማት ሂደትን ያካትታል ወይ?

የኢ.ሥ.ሥ.ሕግ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 36

ይህም ለአቤቱታ አቅራቢው የተሰጡ መብቶች

ሀ) ምስክርነት የመስጠት፤

ለ) ምስክሮችን እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማቅረብ እና የማሰማት፤

ሐ) ለተቋሙ የቀረቡ ማስረጃዎችን የመስማትና የመመርመር እንዲከበሩ ይደረጋሉ ወይ?

18. የአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ይዘትና አኳኋን በተመለከተ በተቋማችሁ ተግበራዊ የሚደረገው አሰራር ምንድ ነው?

ሐ. ከሰርኩላር ጋር ተያያዥ የሆኑ ጥያቄዎች

19. ተገልጋዮች በሕግ የተሰጣቸውን መብት ወይም ጥቅም የሚገድቡ ሰርኩላሮች አሉ? ይህ ማለት ከአዋጅ ወይም ከደንብ ወይም ከመመሪያ ጋር የሚጋጩ ሰርኩላሮች አሉ? አስፈላጊነታቸው ምንድ ነው? ይህን ለማስተካከል በተቋማችሁ ምን ታስቧል?

አባሪ ሁለት

በጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተሰጡ የውሳኔ መዝገቦች ዝርዝር

የዋጋ አተማመን ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ፣ አብናት ስቲል ማኑፋክቸሪንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር (አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)

1. የታሪፍ አመዳደብ ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ፣ SHENGWEI HOME TEXTILE MANUFACTURING PLC (አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)
2. የዋጋ አተማመን ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ፣ አብደላ ኡመር (ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)
3. የዋጋ አተማመን ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ፣ አብደላ ኡመር (በዋናው መስሪያ ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)
4. የዋጋ አተማመን ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ፣ መሰረት ገበየሁ መላኩ (የሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)
5. የታሪፍ አመዳደብ ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ፣ (ADVANTECH NETWORK & COMM. SYSTEMS PLC (አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)
6. የዋጋ አተማመን ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ፣ ፅዮን ንጉሴ (ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)
7. የታሪፍ አመዳደብና የዋጋ አተማመን ላይ የቀረበ ቅሬታና የተሰጠ ውሳኔ ((የሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የተወሰነ)